ለሚዲያ

**ለማቀድ የሚረዳ**
ማርች 13 2020

**ለበለጠ መረጃ**
Susana Castillo (EOM) – (202) 727-5011; susana.castillo@dc.gov

# ከንቲባ ባውዘር የዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያን የመንግሥት አሠራር ሁኔታ ለወጡ

**(ዋሺንግተን ዲ.ሲ.)** ከንቲባ ሚሪል ባውዘር የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ19) ስርጭትን ለመግታት ከሰኞ ማርች 16 ጀምሮ እስከ ማርች 31የዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ የመንግሥት አሠራር ሁኔታን ይለወጣሉ።

በሚዲያ ተገኝነት ዛሬ ከሰአት በ4:00ሰአት ከንቲባዎ ስለነእነዚህ መመሪያዎች ይናገራሉ:

- ከሰኞ ፣ ማርች 16 ጀምሮ እስከ ማክሰኞ ፣ ማርች 31 ድረስ የዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ ዋና ዋና እና ወሳኝ አገልግሎቶችን አቅርቦትን ለመቀጠል በማሰብ ኤጀንሲዎች በወሰኑት የጊዜ ሰሌዳ በቴሌኮሙኒኬሽን ሥራቸውን ያከናዉናሉ፡፡ አንዳንድ የመንግስት ስራዎች ሙሉ በሙሉ በሩቅ ይከናወናሉ ፣ ሌሎች አገልግሎቶች በሕዝባዊ ሕንፃዎች ውስጥ መከናወናቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን ነገር ግን አሠራር ሁኔታዎች ይለወጣሉ፡፡ ስለ ዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ የሥራ ሁኔታ የበለጠ ለመረዳት ሠራተኞች ጠዋት በ10 ሰዓት የስልክ ስብሰባላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል ፡፡ የዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ መንግሥት ረቡዕ ኤፕሪል 1 ቀን መደበኛ ሥራውን ይቀጥላል፡፡

- ከሰኞ ፣ ማርች 16 ጀምሮ እስከ ማርች 31 የዲሲ የህዝብ ትምህርትቤቶች (ዲሲፒኤስ) የርቀት ትምህርት ይጀምራሉ። በዚያን ጊዜ ተማሪዎች ለት/ቤቶች ሪፖርት አያደርጉም።

    - ሰኞ ፣ ማርች16 - መምህራን እና ሰራተኞች የርቀት ትምህርትን ለማቀድ ወደስራ ሪፖርት ያደርጋሉ።
    - ማክሰኞ ፣ ማርች 17 - እስከ አርብ ማርች 20 እና ሰኞ ፣ ማርች 23 የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ፣ አስተማሪዎች እና ሠራተኞች የአመቱ አጋማሽ እረፍት ይወስዳሉ፡፡ በኤፕሪል ውስጥ የአመቱ አጋማሽ እረፍት አይኖርም።
    - ማክሰኞ ፣ ማርች 24 - አርብ ፣ ማርች 27 እና ሰኞ ፣ ማርች 30 እና ማክሰኞ ማርች 31 ተማሪዎች በሩቅ ትምህርት ይሳተፋሉ።
    - ረቡዕ ፣ ኤፕሪል 1 ትምህርት ቤቶች መደበኛ ሥራቸውን ይጀምራሉ።
    - ቻርተር ት / ቤቶች ይህንን መመሪያ እንዲያከበሩ ይመከራል፣ ረቡዕ ኤፕሪል 1 ት / ቤቶች ይከፈታሉ ፡፡ ይሁንና የመምህራን የአቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ የርቀት ትምህርት ዝግጅት ፣

እና የአመቱ አጋማሽ እረፍት ውሳኔዎች በየአካባቢያዊ የትምህርት ኤጀንሲ ሊለያዩ ይችላሉ
፡፡

o ዲስትሪክቱ ከሰኞ ፣ ማርች 16 ፣ እስከ ማርች 31 ፣በሥራ ቀናት ከ ጥዋቱ 10:00 - ከስአት 2:00 የምግብ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የምግብ ጣቢያዎች ዝርዝር በcoronavirus.dc.gov. ይለጠፋሉ።

o የዲሲ የህዝብ ቤተመጽሐፍት ሰኞ ማርች 16 የሚዘጉ ሲሆን ረቡዕ ኤፕሪል 1 ይከፈታሉ ፡፡

**መቼ**

ዓርብ ፣ ማርች 13 ፣ በ 4 ሰዓት ላይ

**ማን**

**ከንቲባ ባውዘር**

የአስተዳደሩ ባለሥልጣናት

**የት**

University of the District of Columbia Community College
Multipurpose Room
801 North Capitol Street, NE
***ቅርብ የሆነ የሜትሮ ጣቢያ: ዩኒየን ጣቢያ***

በስብሰባው ላይ ለመገኘት ፍላጎት ያላቸው የሚዲያ ጣቢያዎች ሁሉም በ press@dc.gov እንዲመዝገቡ ተጠይቀዋል ፡፡ ዝግጅቱን በመስመር ላይ ለመመልከት ፣ mayor.dc.gov/live ይጎብኙ ወይም በሰርጥ 16 (DCN) መመልከት ይችላሉ።

###

**ማህበራዊ ሚዲያ**

Mayor Bowser Twitter: @MayorBowser
Mayor Bowser Instagram: @Mayor_Bowser
Mayor Bowser Facebook: facebook.com/MayorMurielBowser
Mayor Bowser Website: mayor.dc.gov
Mayor Bowser YouTube: https://www.bit.ly/eomvideos

ስለ **የኮሮና ቫይረስ ኮቪድ**19 ሊያስከትል ስለሚችለው ጉዳት የየዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ መንግስት ዝግጅት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።